# ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይረዳም

ነጻነት ዘገዬ

ይህች ጽሑፍ በዚያን ሰሞን ተልካ በብዙዎች ድረ ገፆች ወጥታ ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን ከወቅቱ አንጻር ተቀባብታ ቀርባለችና ብትነበብ ቅር የምታሰኝ አይመስለኝም፡፡ እናም በተለይ በፊተኛው ጊዜ ያላነበባችሁ አሁን ብትመለከቷት አዳዲስ ነገሮችን ጭምር ታገኙባታላችሁ፡፡ ለምሳሌ አዲሱ አበበ የምንለው የቪኦኤ ጋዜጠኛ ሰሞኑን አሳየው በተባለው የማይገባ ምግባር ላይ አቃቂር ቢጤ ተካትቶባታል፡፡ የዚህን ጋዜጠኛ ድርጊት ሙሉ ጥንቅር ለመመልከት የኢትዮጵያን ሪቪው ድረ ገፅን መቃኘት ይቻላል፡፡ እንደ መጽሐፉ ቃል የሚወጣ እንጂ የሚገባ ነገር ሰውን ስለማይጎዳ ደግመንም ቢሆን በጋራ እንመልከታት፡-

በሰሞነኛ ሀገራዊ የፖለቲካ ትኩሳትና ያን ተከትሎ ሊከሰት ይችላል ብዬ በጉጉት በምጠብቀው የማይቀር የለውጥ ማዕበል ምክንያት ስሜን የምቀይርበት ዘመን እየደረሰ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ ‹ነጻነት ዘገዬ› በሚለው ስሜ የዘለቅሁበት የዓመታት ብሶትም አንገቴ ደርሷል፡፡ ሲያላዝን የሚኖር ውሻ ብቻ ነው፤ እኔ ደግሞ ሰው ነኝና ከእንግዲህ የሀዘንና የመከራ ዘመኔ ወደ ታሪክነት መለወጥ ይገባዋል፡፡ እናም ‹ወርቁ ሞላ› ወይም ‹ማሩ ዘነበ› ወደሚል አዲስ የብዕር ስም እንድሻገር በሀገርም በውጪም ያላችሁ ወገኖች ሊጋራ የተሻለ ኀልውና የምትችሉትን ሁሉ አድርጉ - ዝምታና ሞኝነት ለእንዶድም አልበጀት፡፡ ወያኔዎችም ራርተውልን በጉጉት የምንጠብቀውን የአንድያ መሪያችንን  መርዶ በቶሎ እንዲነግሩን መንፈስ ቅዱስ ይርዳን፡፡ እንደነሱ፣ የመለስን ሞት ቢናገሩ ዓለም የምታልፍ መስሏቸዋል፡፡ እርግጥ ነው ዓለም አትለፍ እንጂ የመለስ ሞት ከሚገለጽባት ማግሥት ጀምሮ ኢትዮጵያ በአዲስ መልክ መገንባት ትጀምራለች፡፡ ፍራቻቸው ያ ነው፡፡ ግን ደግሞ የፈሩት መድረሱ የጠሉት መውረሱ ያለ ነውና መለስን ቋንጣ አድርገው ሊያስቀምጡት ስለማይችሉ የግዳቸውን ይናገራሉ፡፡ ያኔ የቀዘቀዘው መጋል ይጀምራል፤ የዛለውም መበርታት ይይዛል፡፡ ወያኔዎች ከባህልም ከወግና ልማድም ከሃይማኖታዊ ትውፊትም ከሞራልም ስለወጡ እንጂ አስከሬን አጋድሞ ዓለምን መቅጨት ቀርቶ ምግብ እንኳን መቅመስ እጅግ ነውር ነበር፡፡ ባገራችን ሰው ከሞተ በኋላ ሳይቀበር እህል ውኃ አይቀመስም፡፡ እነሱ ግን ሬሣ አጋድመው በጮማና በውስኪ ይምነሸነሹ ይዘዋል፡፡ ለነገሩ ከሞላ ጎደል ሁላቸውም በጊዜ ሰጪ በሽታዎች የተለከፉና ሞታቸውን የሚጠባበቁ በአካልም በመንፈስም ህሙማን ስለሆኑ ለሞት ከነሱ ይበልጥ የቀረበ የለም፤ ስለሆነም ሬሣ አጋድሞ መብላትና መጠጣት ጉዳያቸው አይደለም - በሬሣ ላይስ አይደል እየተረማመዱ ወደ አራት ኪሎ የመጡት፡፡ ችግራቸው የአምልኮት ያህል ሽቅብ ያዳኑት መለስ ሲቀበር የሚፈጠረው የሥልጣን ክፍተት፣ ክፍተቱም የሚያስከትለው ሽኩቻ፣ ሽኩቻው የሚያመጣው የርስ በርስ ዕልቂትና በተጓዳኝ የሚከሰተው አሁን በ‹ሆድ ይፍጀው› እየተንተከተከ ያለው የሕዝቡ አመጽ ነው፡፡ ያን መጻኢ የማይቀር  ማዕበል አያልፉትም፤ እንደማያልፉትና ዕድሜያቸው በጣም እያጠረ መምጣቱን ተረድተዋል፡፡ ስለዚህ ሬሣ አቅፈው መኖርን መርጠዋል ማለት ይቻላል፤ ይቺ ‹ዕረፍት ላይ ነው፤ ዓመት ፈቃድ ወጥቶ ነው፤ የሕክምና ፈቃድ ላይ ነው…ቅብጥርሶ ቅብጥርሶ› እሚሏትን እርስ በርስ የምትጋጭ ማጨናበሪያ ይተዋትና ሄደው ሌላቸውን ይብሉ፡፡ በመለስ ፍርሀት እንኳንስ ለ46 ቀናትና በጤናው ከወንበሩ ለአንዲት ቀንም ቢሆን ዘወር አይልም - እንዲሁ አየሩንም ፀሐዩንም ዛፍ ቅጠሉንም  ስለሚፈራ እንጂ የሚያሰጋው ሰው እንደሌለና አጠገቡ ያሉትን ሁሉንም ወደዕቃነት እንደለወጣቸው ዘንግቶት እንዳልሆነ ግን ልብ ይሏል፡፡

የሆነ ሆኖ ጊዜው የአፄ ምንሊክን ዘመን ስላልሆነ ሬሣን በመደበቅ ሊጓዙ በደፈሩበት መንገድ መጓዙ ብዙም አያዛልቃቸውም፡፡ ተጨቋኝ ወገኖች ግን ነቃ ማለት አለባቸው፡፡ እርግጥ ነው በባህላችን ሰው ነፍሱ ከመውጣቱና እንዲያውም ሞቶ ተቀብሮም ዐርባና ተዝካሩ ከማለፉም በፊት በዚያ ሰው ቅርስና

ውርስ ላይ በድን ሬሣን አጋድሞ መነታረኩ ትዝብት ላይ እንደሚጥል ሁሉ መለስ መሞቱ ገና በይፋ ሳይገለጽና ሥርዓተ ቀብሩ ሳይፈጸም ከተቃዋሚም ሆነ ከሕዝቡ ምንም ነገር ባይከሰት የሚጠበቅ እንጂ ፍርሀት ወይም ተላላነት እንዳልሆነ ለወያኔያውያን መጠቆም እፈልጋለሁ፡፡ ጨዋ ባህል ያለን ሕዝብ ነን፡፡ ጽንስ አለጊዜው አይወለድም፤ ከጊዜውም አያልፍም፡፡ ዋናው ቁም ነገር በኢትዮጵያ ላይ ለተሾመው የዲያብሎስ መንጋ ዋና የጦር አበጋዝ የነበረውና በመለስ ጫንቃ ላይ ዐርፎ የነበረው የኢጋንንት መንፈስ ከዙፋኑ መነሳቱ በገሃድ ይታወጅ፤ ከዚያ በኋላ ግን ሕዝቡ የተቀማውን ወንበር ለማስመለስ በጎበዝ አለቃዎቹ እየተደራጀ ትግሉን የሚቀጥል መሆኑ የማይቀር ማኅበረሰብአዊ ክስተት ነው፡፡ ማንም ወደደ ጠላ 2005ዓ.ም የነጻነት ዓመት ናት - ስድስተኛው ስሜቴ የሚነግረኝ ይህንን ብሥራት ነው፤ ለነገሩ ይህም ቢሆን እግዜር (ማድረግ) ከሚችለው በታችና እኛም (ሊደረግልን) ከሚገባን በላይ ነው - ብዙ ተረግጠናልና፡፡ (ይቺ ዐረፍተ ነገር መታሰቢያነቷ ለቴዲ አፍሮ ይሁን)

እንደውነቱ ጥሩ ዜና ነው፡፡ አቶ መለስ ማረፉ እጅግ በጣም ጥሩ ነው፡፡ ሰው ሲደክመው ማረፉ ያለና የነበረም ነው፡፡ በተለይ አቶ መለስ የማያዳግም ታላቅ ዕረፍት ያስፈልገው ነበር፤ ብዙ ደክሟል፤ አልሳካ ብሎት እንጂ የሚወዳት ብቸኛ ሀገሩን  ኢትዮጵያንና የሚወደንን ኢትዮጵያውያንን በቀን ሦስት ጊዜ ከመመገብ ጀምሮ የጠፈር ቱሪስቶች እንድንሆንለት ለማስቻል ብዙ ጥሯል፡፡ ማንም ሊያውከው በማይችልበት በዚህ መልክ እንዲያርፍም ብዙዎቻችን ላለፉት በርካታ ዓመታት ስንጸልይለት ቆይተናል፡፡ ይሄውና ጸሎታችን ሠምሮ ዐረፈ መባልን መስማት ከጀመርን ሣምንታት ተቆጠሩ - እየተወራበትና እየተወራልን ያለው ነገር ሀሰትም ቢሆን ፈጣሪ እውነት ያድርገውና ይህን ቆሞ ያልጠቀመንን ብቻ ሳይሆን እኛንና ሀገራችንን በቁማችን እንጦርጦስ ያወረደንን ክፉ ሰውዬ በቶሎ ይገላግለን፤ ሰው ይሙት ባይባልም ከክፋት ሥራው አንጻር ሞትም ሲያንሰው ነውና ይህን ሰይጣን ከነግብረ በላዎቹ ያንሳው፤ ሁሉም ደማችንን እንደ አልቅት ተጣብቀውብን መጥጠው አብጠዋልና እየፈነዱ ይሙቱ፤ ሞት በነሱ አልተጀመረምና እንደመኽገር እየፈረጡ ይህችን ዓለም እስከወዲያኛው ይሰናበቱ፤ ጎያው አምላክ ይስማንና የሥራቸውን ይስጣቸው፡፡ ለማንኛውም ግን ለዚህም ላበቃን እግዜር እንዴት ተብሎ ነው ምሥጋና የሚቀርብ? ብቻ ስሙ የተባረከ ይሁን፡፡ ከተመስገን ሌላ ምን ይባላል? ለዘላለሙ የተመሰገነ ይሁን፡፡

አንድ የደስታ ኣጋጣሚ ሌላ የሀዘን ኣጋጣሚ ሊፈጥር እንደሚችል መረዳት ግን ይህችን ወርቃማ ጊዜና ዕድል በከንቱ እንዳናባክናት ልብ እንድንል ያደርገናል፡፡ በመሠረቱ በሊቀ ሣጥናኤል አቶ መለስ ዜናዊ ዜና ዕረፍት ብዙም መደሰት ተገቢ አይመስለኝም፡፡ ማረፉ የሚያስከትለውን ሀገራዊ በረከት በማጤን ከጉዳቱ ጥቅሙ ይበልጣል ብለን እንጽናና እና ዜና ዕረፍቱን በደስታ እንቀበል እንደሆን እንጂ በሰው ሞት መደሰት ሞራላዊም ሆነ ሃይማኖታዊ አይደለም፡፡ ፈጣሪ አዘዘው፤ የታዘዘውን ፈጸመ፤ ና ሲለው ሄደ - በርግጥም ሄዶ ከሆነ፡፡ የመለስ ጥፋት የመላላክ እንጂ የራሱ አይመስለኝም፡፡ ‹እግዜር ሲቆጣ ሽመል አይቆርጥም ያደርጋል እንጂ ነገር እንዳይጥም› እንላለን፡፡ ጥፋት አለብን፡፡ ጥፋቱ አሁንም ድረስ አለብን፡፡ ከጥፋት እንመለስ፡፡ ያኔ ከጫፍ የጀመረው አብዮት እስከታች ይወርዳል፡፡ ሳናስበው ከላይ የወረደ ቡራኬ እያየን ነው፤

ፈረንጆች surgical operation የሚሉት ንዑስ ሐረግ አላቸው፡፡ በሁለት መንገድ ይጠቀሙበታል -በሕክምናውና በወታደራዊው ዘርፎች፡፡ የሕክምናውን ሁሉም ያውቀዋል፡፡ በወታደራዊው ዘርፍ ሰርጂካል ኦፐሬሽን ሲሉ ልክ እስራኤል እንደምታደርገው አንድን ሞት የሚገባውን ሰው ወይም መውደም አለበት የተባለን ዒላማ በልዩ ሥልት በአካባቢው የሚገኝ ሌላ ሰውና ነገር ሳይጎዳ ለይቶና አነጣጥሮ

በማጥቃት ዓላማን ማሳካት ማለት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ የማጥቃት ሥልት ከብዙ ወታደራዊ ኪሣራና ወጭ ይታደጋል፡፡ ትልቅ አደጋንም ይሠውራል፡፡

በኢትዮጵያ እግዚአብሔር ይሁን ወይም ገና ወደፊት የሚታወቅ ሥውር ኃይል - ልዩ ቴክኖሎጂም በመጠቀም- (መጠርጠር ነው) ባደረገው ሰርጂካል ኦፐሬሽን ይህ መፃጉዕ ሰውዬ የማይቀር ዓለማዊ ሒሳቡን አግኝቷል፤ የነፍሱን እዚያው ያወራርድ፡፡ ባልተጠበቀው ሁኔታ የተወነባበዱት ወያኔዎች ቤታቸውን እስኪያስተካክሉና የተዝረከረከውን ነገር ሁሉ እስኪያጸዳዱ ቢደብቁትም እውነቱ እውነት መሆኑን ከጥርጣሬ በላይ እየተረዳን መጥተናል፤ መቼም ዱብ ዕዳ ነው የሆነባቸው፤ የሆነብንም፡፡ ከእንግዲህ የመለስ ፀሐይ ጠልቃለች፤ ከእንግዲህ እኛም ካወቅንበት የወያኔ ፀሐይ ባጠቃላይ ጠልቃለች፡፡ የኛ ፀሐይ እንድትወጣ ግን ገና ብዙ ልፋት ይጠብቀናል፤ የነጻነት ጎሕ አሁን ነው መቅደድ የጀመረው፡፡ በመጀመሪያ በተበጣጠቀ ሁኔታ ውስጥ የሚገኘው የተቃዋሚ ጎራ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ወደ ማዕከል መሰባሰብና በአፋጣኝ መነጋገር ብቻ ሳይሆን ወደ ተግባራዊ እርምጃ መግባት ያስፈልገዋል፤ ይህች ዕድል የጋለች ብረት እንደማለት ነች፡፡ ካልተጠቀሙባት ብረቱ እንደገና ይጠጥርና ለመቼውም ሊያስቸግር ይችላል፡፡ የተቃዋሚው ጎራ እንደ እስካሁኑ ገና ባልተገኘ ሥልጣን የሚቀራቆስና የሚሻኮት ከሆነ ይህችም ዕድል እንደስካሁኖቹ ታመልጣለች፡፡ ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ፡፡

እኔ በበኩሌ እንደሚከተለው እራገማለሁ፤

ከእንግዲህም ሆነ አሁን በዘርና በጎሣ እንዲሁም በሃይማኖት የሚደራጅ ጥቁር ውሻ ይውለድ፤ ዘር አይውጣለት፡፡ ከእንግዲህም ሆነ አሁን የሕዝብን ስቃይ ለግል ጥቅሙና ለሥልጣን ፍላጎቱ ማርኪያ የሚያውል ጥቁር ውሻ ይውለድ፤ ዘር አይውጣለት፡፡ ከእንግዲህ ከሕዝብ ሰቆቃና ችግር በፊት የራሱን የሥልጣን ሱስና የሀብት ማከማቸት ቁሣዊ አራራ የሚያስቀድም ዜጋ ጥቁር ውሻ ይውለድ፤ ዘር አይውጣለት፡፡ ከእንግዲህ ወደ ጤናማ አስተሳሰቡ ተመልሶ ይህን በቁሙ የሞተ ሕዝብ ለማዳን የማይሠራ ዜጋ፣ ይህችን በውርደት መንገድ እየነጎደች ያለች ሀገር ለማንሳት የማይተጋ ዜጋ ጥቁር ውሻ ይውለድ፤ ዘር አይውጣለት፡፡ ከእንግዲህና አሁን በንግድ ሰበብ ሕዝቡን እስከመቅኒው ድረስ የሚግጥ ዜጋ ጥቁር ውሻ ይውለድ…፡፡ ከአሁን በኋላ አንተ ትግሬ አንቺ አማራ አንተ ኦሮሞ እሱ ጉራጌ እነሱ ከምባታ … በሚል የዘረኝነት ወያኔያዊ ልክፍት ተጠምዶ ወገንን ከወገን የሚለይ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ጥቁር ውሻ ይውለድ፡፡ ከአሁን በኋላ የተቀበረን እየቆፈረ ባለፈ በደልና ጥፋት ቋሚን የሚወቅስ ሰው ጥቁር ውሻ ይውለድ፡፡ ከአሁን በኋላ ከኢትዮጵያዊነት የጋራ መገለጫ በፊት በነገዱና በጎሣው ወይም በሃይማኖቱና በቋንቋው ሰውን እየለዩና እያንጓለለ ሥራ የሚቀጥር ወይ የሚያስቀጥር፣ ከ‘meritocracy’ ይልቅ ማንኛውንም ዓይነት ያልተገባ ‘discrimination’ የሚያራምድ ጥቁር ውሻ ይውለድ፣ ዘር አይውጣለት፡፡ ይህን እርግማን እግዚአብሔር እንዲቀበለው የምትደግፉኝ ጸልዩ፡፡

በኢትዮሚዲያ ድረ ገፅ ከቀረበ አንድ የእንግሊዝኛ ዘገባ የተረዳሁት አሳሳቢ ችግር አለብን፡፡ ይሄውም የመለስን ማረፍ ተከትሎ ሊከሰት ስለሚችል ሁኔታ ነው፡፡ የመለስ ማረፍ ብቻውን ሊያዘናጋን እንደማይገባውና እንደማይችልም በዚህ ዘገባ ተገንዝቤያለሁ፡፡ የነብር ዐይን ወደ ፍየል የፍየል ዐይን ወደ ቅጠል ይባላል፡፡ እኛ በመለስ ሞትና በሀገር መገላገል ላይ ስናተኩር የሀገሪቱ መሠሪ ታሪካዊ ጠላቶች ምን እየሠሩ እንደሆነ መገመት እንዳያቅተን መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡ እርግጥ ነው መለስ ትልቁ ሞጂሌ ነበር፤ ትልቅ ሞጂሌ ከነሰንኮፉ እንደተገላገልን ልንቆጥር እንችላለን፤ ግን ብዙ ሞጂሌዎች ከነሰንኮፋቸው አሉ፡፡ በአምባገነናዊ ሥርዓቶች ዋናው ቁንጮ ሲገረሰስ እንደተናጋሪ ዕቃ የሚቆጠሩት በሥሩ ያሉት ተከታዮች የሚገቡበት እንደሚያጡና እንደሚደነጋገጡ ግልጽ ነው፡፡ ከኛው ታሪክ ብናይ አፄው ሲወርዱ ሁሉም ነገር ተንኮታኮተ፤ መንግሥቱ ሲወርድ ሁሉም ነገር ተንኮታኮተ፣ አሁንም መለስ ሲሞት - ስብሃት ለአፉ ያህል

ምንም ችግር እንደማይኖር እንደወያኔያዊ የመወሻከት ልማዱ ይዘላብድ እንጂ - ሁሉም ነገር ይንኮታኮታል፡፡ እሙኑኝ ተቃዋሚም ባይኖር (ካለንም እሰዬው ነው) እርስ በርሳቸው ይባላሉ፤ በዚያም ሳቢያ ውስጣዊ አብዮት ይፈነዳል፤ በዚያውም ‹በንነው ይጠፉሉ› የተባለው ትንቢት እውን ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል፡፡ በመጥፎ ምግባር የበሸቀጡ፣ በሃይማኖት የበከቱ፣ ከባህልና ወጋችን ያፈነገጡ፣ … በመሆናቸው ቀሪዎቹ ወያኔዎች ከእንግዲህ የሚያገግሙበት አጋጣሚ ጨርሶውን የለም - አሁንም ልድገመው ተቃዋሚ እንኳን ባይኖር፡፡ የማይምር በትር ታዞባቸዋል ባይ ነኝ፡፡

ፈጣሪ ፍጡሩን ጥሎ አይጥልም፡፡ ተቃዋሚዎች ለራሳችሁ ስትሉ ተባበሩና ይህን ዕድል ተጠቀሙ፡፡ የሩቅ ተኩስ ያንጀትን አያደርስም፡፡ ከአሥራ ምናምን ሺህ ማይሎች ርቀት ላይ በሚተኮሱ ስሜታዊ ቃላትና የአቋም መግለጫዎች እንዲሁም ጋዜጣዊ ሀተታዎች የጠላትን የተደበቀ ገመና ማጋለጥ ይቻል ይሆናል እንጂ ዝምቡን እሺ ማለትና የጭረት ያህልም ብትሆን ማቁሰል አይቻልም፡፡ አሁን ያለን የጠላት መንጋ ደግሞ ለቋንቋ ደንታ የለውም፤ ስትሳደብ ውለህ ብታድር፤ በሥነ ጽሑፍ ርቃቅትህ እንደነ ሼክስፒርና ሎሬት ጸጋዬ ስትቀኝ ውለህ ስትቀኝ ብታድር በልፋትህ ይስቅብሃል እንጂ ጉዳዩ አይደለም፡፡ ነገሩ የመጻፍ ሳይሆን የመተኮስና ዒላማን የመምታት ነው፡፡ በሀሰትና በዕብለት ተጠንስሶ ያደገና ለአካለ መጠን የደረሰ ወያኔያዊ ውድብ(ድርጅት) በስድብና በዘለፋ እንደጢስ በንኖ ይጠፋል ማለት ቀልድ ነው፡፡ አየነው፡፡ በጩኸት ብዛት ወያኔ አንድ ኢንች እንኳን ወደኋሊት መሄድ ቢችል ኖሮ ባለፉት 21 ዓመታት ውስጥ እኔ ብቻየንና ከጓደኞቼ ጋር በየመሸታ ቤቱ በጮኽሁት በብዕሬ በሞነጫጨርኩት የብሶት ጎርፍ ብቻ ተጠራርጎ ቀይ ባሕርን አልፎ ሕንድ ውቅያኖስ ውስጥ በገባ ነበር፡፡ የማይሆን አይሆንም፤ አንልፋ፡፡ ወደተግባር እንግባ፡፡ ወደተግባር የሚያስገባን ኃይል ይኑር፤ ጬኸታችን በቲዮሪ ብቻ ሳይሆን በተግባር ይደገፍ፡፡ ጉዳዩ ቀድሞ መገኘት ነው እንጂ በርግማንና በስድብ የሚጠፉ ጠላት የለም፡፡ ስድብና ነቀፋ የአምባገነኖች የደንብ ልብስ ነው፡፡ የሚገርማቸው ይልቁንስ ስለነሱ መልካም ነገር ቢነገርላቸው ነው - ያልፈጠረባቸውን፡፡

ወደኢትዮሚዲያ ሥጋት ልመልሳችሁ፡፡ አሁንና ከ93ዓ.ም ወዲህ ሕወሓትን እየመሩ ያሉት እውነተኞቹ የትግራይ ተወላጆች ሳይሆኑ ኤርትራውያን ናቸው፡፡ በመሠረቱ በበኩሌ የየትኛውም ክልል ተወላጅ ቢሆኑ ሃሳቡ አይበላኝም፡፡ ከኬንያ ሄዶ አሜሪካንን እያስተዳደረ የሚገኘው የዓለማችን ዜጋ የተወሰኑ የጥራት መሥፈርቶችን በማለፉ እንጂ እንደኤርትራውያኑ ሠርጎ ገቦች በሕግ አልባነት የጫካ ሕግ እየተመራ አይደለም፡፡ እነዚህኞቹ ግን በአንጻራዊ ሁኔታ ለኢትዮጵያ ደግ የሚያስቡትን የትግራይ ትግሬዎች በቂምና በበቀል መንጥረው በማባረር ሁሉንም በእነሱ ቁጥጥር አድርገዋል፡፡ ይህ አደገኛ አካሄድ ግዘፍ እየነሳ ሄዶ በአሁኑ ወቅት አጠቃላዩ የሀገራችን ሕልውና በኤርትራውያኑ መዳፍ ሥር ያለ ይመስላል፡፡ ይህ የፈጠጠ እውነት አራት ኪሎ ቤተ መንግሥት ላይ ተገሽሮ እየተንጎማለለ እኛና ተቃዋሚዎች በመለስ ሞትና በማያስማሙን ጉዳዮች ዙሪያ ብቻ መተብተባችን ደግ አይደለም ብቻ ሳይሆን አንዳች ነገር የተዘረብን ነው የምንመስለው፡፡ እንደገና የመፈጠር ያህል አስተሳሰባችንንና አመለካከታችንን ልንለውጥ ይገባናል፡፡ እነ ንዋይ ገ/አብ፣ ሳሞራ የኑስ፣ ብርሃኔ ገ/ክርስቶስ፣ ዶር. ቴዎድሮስ አድሃኖም፣ በረከት ስምዖን … ሁሉም በአሁኑ ወቅት ያሉት የወያኔ ባለሥልጣናት ኤርትራውያን መሆናቸው የአጋጣሚ ነገር ሳይሆን መለስ ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ ለሚያደላላት የቀድሞ ክፍለ ሀገራችን ኤርትራ ያለውን አድልዖና አመኔታ እንዲሁም የመሀል ሀገሩን ሰው(የትግራይን ትግሬ ጭምር) ምን ያህል እንዳንጓለለን ያመለክታል፡፡ የመለስ ማረፍ የምዕራፍ አንድ መዝጊያ ነው፤ ከባዱና ብዙ ትዕግሥትና ትጋት የሚጠይቀው ምዕራፍ ሁለት አሁኑኑ መቀጠል አለበት፡፡ እነዚህን በመለስ ጥላ ሥር መሽገው የነበሩ ውሉደ አጋንንት መመንጠር የሚቻለው ልዩ ሥልት በመንደፍ ነውና ይህ ነገር ይዋል ይደር የሚባል አይደለም፡፡ የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ በተቃዋሚው ጎራ ታውጆ የ24 ሰዓት ሥራ መሠራት አለበት፡፡ ኋላ እንዳይቆጨን!

አሁን ለወሬ ብዙ ጊዜ ልንሰዋ አያስፈልግም፡፡ ስንፈራው የነበረውን ጦርነት ግማሹን ያህል እግዜር ወይም ያላወቅነው ሌላ ኃይል ተዋግቶልናል፡፡ የሚቀረው ድሉን መሰብሰብ ብቻ ነው፡፡ ድሉን መሰብሰብ የምንችለው ደግሞ እንደእስከዛሬው በወሬና ዛሬ ተገንብቶ ነገ በሚፈርስ ጉባኤና ንቅናቄ ምሥረታ በመጠመድ ሳይሆን በተግባራዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ሲያጎርሱት የማያላምጥ የሞተ ብቻ ነው፡፡ ልዩ ኃይል ልዩ ጉርሻ አጉርሶናልና እንጠቀምበት፡፡ ሦርያውያን ይህን መሰል ዕድል ቢያገኙ ምንኛ በታደሉ? እኛ ከጸሎትና ምናልባትም ከዚያ ሣተና ወጣት ጋዜጠኛ አበበ በለው አኩሪ ተጋድሎ በስተቀር ብዙም ሳንለፋ አናቱን በማያዳግም ሽመል በርቁሶ ጥሎልናል፤ ከእንግዲህ ያለብን ግዴታ ገበር ገበሩን እያሳደዱ ለፍርድ ማቅረብ ነው፡፡ በነገራችን ላይ ይ አዲሱ አበበ የሚሉት ጋዜጠኛ ይህን ያህል ባለጌ ኖሯል እንዴ? ኧረ ምከሩት! ዛሬ በኤልየስ ክፍሌ ድረ ገፅ ላይ ስለእርሱ ያነበብኩት አስከፍቶኛል፡፡ ዐይጥ ወልዳ ወልዳ ጅራቷ ላይ ስትደርስ ሲጥ እንደተባለው አትሁን በሉልኝ፡፡ ይሄ መጠጋትና ማግኘት እኮ ዕዳ ነው፡፡ ወያኔን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማገልገል መጨረሻው እንደማያምር እያስረዳችሁ አሁኑኑ መልሱት፡፡ ትዕቢትና ጉራ ለመለስም እንዳልሆ ንገሩት፡፡ አይ …  ባላዳምጠውም ከሰዎች አባባል ልክ እንዳልሠራ መጠነኛ ግንዛቤ አግኘቻለሁ፡፡ ጋዜጠኛ ብቻ ሁን በሉት፡፡ ዶላር ሲበዛ እርግጥ ነው አንጎልን ያናፍላል - በእኔ ደርሶ ባላየውም በብዙ ሰዎች አይቻለሁ፡፡ ሪጂስትሮ የሌለው አንጎል ብዙ ገንዘብና ብዙ ዝና ሲመጣበት እንደመቅሰፍት እንጂ እንደበረከት ሊቆጠርለት አይችልም፡፡ ሀብትና ዝና አንዳንዴ ያሳውራል፤ በትዕቢትም ያሳብጣል፡፡ ለዚህም ይመስለኛል ይሄ ጥጋበኛ (የመሰለኝ) አዲሱ አበበ(አበበ የሚለውን ስም ይለውጥ! በወያኔዊ ቅኝት ለሚሰቃይ ሰው የሚስማማ ስም አይደለም) የበኩላቸውን ሀገራዊ ግዴታ ለመወጣት በሚጥሩ ሰዎች ላይ የበላይነትን ለመቀዳጀት በሚመስል ሁኔታ ይዘባነንባቸው የነበረው - እንደሰማሁት፡፡ በሌላ አጋጣሚ ለብቻው ብወቅሰው ጥሩ ነበር፡፡ ግን ሲያድር ይረሳልና አሁኑኑ በድርበቡ ከስህተቱ እንዲመለስ ላሳስበው ፈልጌ ነው በዚህ የተለዩ ጽሑፍ ግርጌ ይህን ያህል ልጠቁም የወደድኩት፡፡ ሁላችንንም ልብ ይስጠን እስኪ፡፡ በተለይ በተለይ ከመጥፎ ሁኔታ ውስጥ እየወጣን ወደ መልካሙ መንገድ እንግባ እንጂ ከጥሩው መንገድ እየተለየን ወደ መጥፎው የብዙዎች ጎዳና እንዳንገባ ፈጣሪ ይጠብቀን፡፡